## አድኚኝ እናቴ

አድኚኝ እናቴ ከስጋ ፈተና
ስጋዬ ከሀጥያት ከቶ አራቀምና
ሸክሜ የከበደኝ ብቸኛ ሆኛለሁ
አትለይኝ ድንግል አደራ እልሻለሁ /2/

የአማኑኤል እናት የተዋህዶ አክሊል
አትጥፊ ከመሃል እንድትሆኝን ሀይል
ምንም ቢበዛብሽ ጉስቁልና
ከኛ ጋራ ከሆንሽ አለን ቅድስና /2/

**አድኚኝ እናቴ**

ተስፋዬነሽና እመካብሻልሁ
ግራ ቀኝም አልል ምርኮኛሽ ሆኛለሁ
ስቅበዘበዝ አይቶ ተስፋ የሰጠኝ
እግዚአብሔር ይመስገን ካንቺ ያስጠጋኝ/2/

**አድኚኝ እናቴ**

በስጋ ደከሜ በነፍሴ እንዳልጠፋ
እማጸንሻለሁ ድንግል የእኔ ተስፋ
ለመንግስቱ ወራሽ እንድሆን አድርጊኝ
መልካም ስራን መስራት እኔን አስተምሪኝ /2/

**አድኚኝ እናቴ**

አንቺ የሌለሽበት ጉባኤው ባዶ ነው
በቁም የደረቀ ሕይወት የተለየው
ከመሃከል ገብተሽ ሙይ የጎደለውን
ሰርጉ ተደግሷል ጎብኚልኝ ጓዳውን/2/

**አድኚኝ እናቴ**

## የእኛ ጌታ የኛ መድኅን

የኛ ጌታ የኛ መድኅን
በቸርነትህ ታደገን
እኛ እንደሆነ ሃይል የለን/2/

ጠዋት ለምልማ ማታ ጠፋች
የሰው ህሊና እያባባች
ዓለም ምኗ ነው የጣፈጠን
እያሳሳቀ የወሰደን

**የኛ ጌታ**

ዛሬ አልች ሲሏት ትጠፋለች
ከነ ተንኮሏ ዓለም ሟች ነች
እሾህ በቅሎባት እሾህ ሆና
በመተላለፍ ሰው ሊያልቅ ነው

**የኛ ጌታ**

ከኛ ጋር ያለው ሃያል ነው
በሥጋዊ ዐይን ባናየው
የጦሩ ብዛት መች ያድናል
የዐለም ጥንስስ ተዋህዷል

**የኛ ጌታ**

እንደሰው ጥበብ ጥበበኛ
እንደሰው ወደር ወደረኛ
እንደ ዓለም ጉልበት ጉልበተኛ
በአምላክ ፊት ሲታይ ሕመምተኛ

**የኛ ጌታ**